SMITTSKYDDSBLAD – PATIENTINFORMATION

AMARINJA – LATENT TUBERKULOS, DÄR BEHANDLING INTE GES

ያደባ የሳንባ ነቀርሳ፥ ለበሽተኛ የሚሰጥ መረጃ

የቅድሚያ መከላከል ህክምና የማይሰጥበት ግዜ። የተላላፊ በሽታ ሓኪሞች መረጃ ልሳን።

የሳንባ ነቀርሳ እንዴት ይተላለፋል?

አንድ ሳምባ ነቀርሳ ያለበት ሰው፥ ቤት ውስጥ ሲስል በሽታውን ሌላ ሰው ላይ ሊተላለፍ ይችላል። ሌላ የሰውነት አካል ውስጥ ያለ ሳንባ ነቀርሳ ኣና ያደባ ሳንባ ነቀርሳ አይተላለፉም። በልጅነት ዕድሜ ውስጥ ያሉ ልጆች በሽታውን ሲያስተላልፉ ማየት የተለመደ አይደለም። ሰዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ለምሳሌ በአንድ ቤት ውስጥ ለረጅም ግዜ አብረው የሚቆዩ ከሆነ በሽታው ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው የመተላለፍ ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?

ነቀርሳው የተላለፈባቸው ሰዎች ሁሉ አይታመሙም። የብዙ ሰዎች ተፈጥሯዊ የበሽታ መከላከያ ኃይል ባክቴሪያው እንዳያድግና እንዳይሰራጭ ሊገታው ይችላል። በዚህ መልኩ ባክቲሪያው ሰውነት ውስጥ እያለ ኣድብቶ ይቀመጣል። በዚህ ሁኔታ የሚገኘው ነው **ያደባ ሳንባ ነቀርሳ** የሚባለው።

ያደባ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ኣይደለም

ከደም ምርመራ (IGRA-Test) ወይም ከቆዳ ምርመራ (Tuberkulintest) ካደረጉ በኋላ ያደባ ሳንባ ነቀርሳ አለብዎት ከተባሉ ሙሉ በሙሉ ጤነኛ ነዎት ማለት ይቻላል። እናም በሽታውን ወደ ሌላ ሰው ማጋባት ኣይችሉም።

ይሁን እንጂ በሕይወት እስካሉ ድረስ በሽታው አንድ ቀን ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት ይኖራል። ሆኖም ይህ የሚያጋጥምበት ዕድል በጣም የመነመነ ሰለሆነ ኣብዛኛዎቹ ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች ህክምና ኣይደረግላቸውም።

በአንዳንድ ሁኔታ የቅድመ መከላከል ህክምና ሊሰጥ ይችላል

አንዳንድ ሰዎች ላይ በሽታው ኋላ ሊከሰትባቸው ይችላል የሚል ስጋት በእጅጉ ካለ የቅድመ መከላከል ህክምና እንዲያደርጉ ይጋበዛሉ። ይህ ህክምና የሚደረገው በቅድሚያ ለህፃናትና ለታዳጊዎች ሲሆን፥ ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ ምክንያትም ይሰጣል። በተጨማሪም የተፈጥሮ በሽታ የመከላከል ኃይላቸው የተዳከመባቸው ለምሳሌ፥ የካንሰር ህክምና የሚያደርጉ፥ ኢንሱሊን የሚወስዱ የስኪር በሽተኞች፥ ከባድ የኩላሊት ችግር ያለባቸው ሰዎችም ይደረግላቸዋል። የቅድመ መካላከል ህክምና አንዳንድ ጊዜ በቅርብ ጊዜ የሳንባ ነቀርሳ ለያዛቸው ሰዎችም ይደረጋል።

ሐኪምን ማነጋገር

ያደባ ሳንባ ነቀርሳ እያለብዎት፣ ሆኖም ግን ሃኪምዎ አሁን ህክምና አያስፈልግዎትም ብሎ ይገምታል። ይህ በእንዲህ እያለ፣ ወደፊት ዘለግ ያለ ሳል (ከሶስት ሳምንታት በላይ)፥ በመኛታ ግዜ በላብ መዘፈቅ፥ ትኩሳትና ያልታሰበ የክብደት መቀነስ ከታየቦት፥ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ ለማድረግ ሐኪሞን ያነጋግሩ። እርጉዝ፡ ወይም ኢንሱሊን የሚወስዱ የስኪር በሽተኛ ከሆኑ፥ ከባድ የኩላሊት ችግር ካለብዎት፥ የካንሰር ህክምና የሚያደርጉ ከሆነ፥ ወይም በሌላ ምክንያት የተፈጥሮ በሽታ የመከላከል ኃይልዎ ከተዳከመም፥ ሐኪምዎን ከማነጋገር ወደ ኋላ ኣይበሉ። እነዚህ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ሊጠቁ የሚችሉበት ዕድል ከፍተኛ ነውና።

የሚገናኙት ሰው አድራሻና ተለፎን (Kontaktuppgifter)

የጤና ጣቢያው ሥም *(Namn på mottagningen)* ……

የጠና ጣቢያው ቴሌፎን ቁጥር *(Telefonnummer/telefontid till mottagningen)* ……